አንድ ሀሳብ

ስለታላቁ ነብይ (ሶ ዐ ወ) ክብር የተከተበ

በሀሰን ታጁ

አንድ ሀሳብ

የሀገራችን ነገር ይገርማል። ነገሮች በፍጥነት ይቀያየራሉ። አዳዲስ አጀንዳዎች በየዕለቱ ይወለዳሉ። አንዱ ባንዱ ላይ ይደራረባሉ። ሰሞኑን አንድ ወንድም በአንድ መድረክ የተነገረ ቪድዮ ላከልኝና ተመለከትኩት፤ የወዳጄን (ሶ ዐ ወ) ስም ያለአግባብ የሚያነሳ ነዉ። “ሰለምቴ” መባላቸዉ መላ ሰዉነቴን አንቀጠቀጠኝ። የዐለሞች ክብር ለዓመታት ሲደፈር ቆንጣጭ ጠፋና ድፍረቱ ወደአይነኬዉ ልዑል (ሶ ዐ ወ) አመራ። “በእንቁላሉ በቀጣሽኝ” ነዉ ነገሩ። ለደቂቃዎች ስሜቴን መቆጣጠር ሳይሳነኝ አልቀረም። ወደሶሻል ሜዲያዉ ጎራ ስል አየሩ ይህ ጉድፍ ሀሳብ ባስነሳዉ አቧራ ታፍኗል። የረሱላችን ወዳጆች በተረዱት ልክ መልስ ለመስጠት ያደረጉት ርብርብ አፅናናኝ። ሰይዲን (ሶዐወ) በዚህ ልክ የተዳፈረ *“ሰዉ”* ዱንያዊ ቅጣቱ ምን እንደሆነ ይታወቃል፤ የአኼራዉን “አለይሰላሁ ቢአህከሚል ሀኪሚን”! በሚለዉ መርህ መሠረት ለአላህ እንተወዉ። “ስለዚህ ጉዳይ ምንትላለህ?” አለኝ ቪድዮዉን ያጋራኝ ወንድም። በሆነዉ ነገር ልቡ ተሰብሯል። ምን ማለት ይቻላል? ነገሩን የምላስ ወለምታ ብቻ አድርገን እንዳናስብ ከዚያ በኋላ የታዩ ራስን የመከላከል አዝማሚያዎች እንቅፋት ሆኑብን። ወለምታም ቢሆን እኮ በጊዜ “ካልታሸ” አያራምድም። አወላግዶ ሊያስቀርም ይችላል። ደግሞም ወለምታዉን ያመነጨዉ “ዐቂዳ” ጉዳይ በእጅጉ ያሳስባል። ብዙዎችን እንደጓያ ምች ሰባብሮ ከጥቅም ዉጭ ሲያደርግ በየዕለቱ እያስተዋልን ነዉ።

በጊዜዉ በሥራ ተወጥሬ ስለነበር መልስ አልሰጠሁትም። ጥቂት ፋታ ሳገኝ እኔዉ ራሴ ደዉየ አጽናናሁትና ወደአዕምሮየ የመጣልኝን ተከታዩን ሀዲስ አብራራሁለት። ተደሰተ። “እባክህን ይህች መልእክት ለሌሎችም ትደርስ ዘንድ ጻፋት” አለኝ። ከጊዜ እጦት በተጨማሪ ስህተት ማነፍነፍ ከመሻኢኾቻችን የተማርነዉ ብሂል ስላልሆነ ለመጻፍ ማንገራገሬ፣ ከራሴም ጋር ብዙ መሚገቱ አልቀረም። ሆኖም አንድም የወዳጅ ነገር ስለሆነብኝ፣ ደግሞም አጋጣሚዉን በመጠቀም ትክክለኛዉን ዐቂዳ ማስተማርና ስለ ወለላዬ (ሶ ዐ ወ) ክብር መከላከል ግድ እንደሆነ ለህሊናዬ በማሳመን የተመጠነች ሀሳብ ለመጫር ወሰንኩ። በእርግጠኝነት የምነግራችሁ ይህችን የሀሳብ ሰበዝ በመምዘዝ ብቻ አንድ ሙሉ መፅሀፍ ማዘጋጀት ይቻላል።

በቪድዮዉ ላስተዋልኩት የዐቂዳ እንከን ብዙ ማለት ቢቻልም ያ ሳያስፈልግ ተከታዩን ሀዲስ በወጉ መረዳት ብቻ በቂ ነዉ፡-

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ، قَالَ: قَالُوا يَا رَسُولَ اللَّهِ مَتَى وَجَبَتْ لَكَ النُّبُوَّةُ؟ قَالَ: «وَآدَمُ بَيْنَ الرُّوحِ وَالجَسَدِ»

አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ፣ ነብይነት የፀናልዎት (የተረጋገጠልዎት) መቼ ነዉ?" በማለት ጠየቋቸዉ፤ "አደም በሩህና በጀሰድ መካከል ሆኖ እያለ" ሲሉ መለሱ።[1]

አደም አካላቸዉ ታንጸ ሩህ ሳይገባላቸዉ ማለታቸዉ ነዉ። ሀዲሱ ሶሂህ ነዉ።

ዑለሞች ሀዲሱን የሚዘክሩት ነብያችን ከሌሎች ነብያት ያላቸዉን ብልጫና ማዕረግ (ኽሳኢስ) ለመዝከር ነዉ። ትርጉሙን በተመለከተ የሀዲስ ተንታኝ ዑለሞች ሀሳብ በሚከተሉት ነጥቦች የሚሸከረከር ነዉ።

[2] أي كان النبي (ص) نبياً وجرت عليه أحكام النبوة من ذلك الحين بخلاف الأنبياء السابقين، فإن الأحكام جرت عليهم بعد البعثة

"ነብዩ መሀመድ ከሌሎች ነብያት በተለየ ሁኔታ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነብይ ነበሩ። የነብይነት ሁክም ፀንቶላቸዋል። ሌሎች ነብያት ግን የነብይነት አህካም የፀናላቸዉ መልእክት ከደረሳቸዉ በኋላ ነዉ።"

[3] بِمَعْنى أَنه تَعَالَى أخبرهُ بنبوته وَهُوَ روح قبل إيجاده الْأَجْسَام الإنسانية

"ማለትም አላህ ነብይ መሆናቸዉን አካላቸዉ ከመፈጠሩ በፊት ገና በሩህ ዓለም ዉስጥ እያሉ ነግሯቸዋል፤"

[4] وَهَذَا إِخْبَارٌ عَنِ التَّنْوِيهِ بِذِكْرِهِ فِي الْمَلَإِ الْأَعْلَى وَأَنَّهُ مَعْرُوفٌ بِذَلِكَ بَيْنَهُمْ بِأَنَّهُ خَاتَمُ النَّبِيِّينَ وَآدَمُ لَمْ يُنْفَخْ فِيهِ الرُّوحُ

"በላይኛዉ ዓለም ዝናቸዉ የታወቀ መሆኑንና አደም ሩህ ሳይገባባቸዉ በስተፊት ነብዩ (ሶዐወ) የመጨረሻዉ ነብይ መሆናቸዉ እንደሚታወቅ ለመግለፅ ነዉ፣"

[5] وكان نبيّا وآدم بين الروح والجسد، وغيره من الأنبياء لم يكن نبيّا إلا فى حال نبوته وزمان رسالته.

---

[1] ቲርሚዚ፣አህመድ፣ሀኪም፣በይሀቂ፣አቡ ኑዐይም፣ጦበራኒና ሌሎችም በተቀራራቢ የቃላት አወቃቀርና ይዘት ዘግበዉታል። ሀኪምንና ኢማም ዘሀቢን ጨምሮ የመስኩ ሊቃዉንት ሶሂህነቱን መስክረዋል። የሸኽ አልባኒን ዉሳኔ ለሚሹም የርሳቸዉም "ሁክም" ተመሳሳይ ነዉ።

[2] العرف الشذي شرح سنن الترمذي 6/5

[3] التيسير بشرح الجامع الصغير 224/2

[4] السيرة النبوية (من البداية والنهاية لابن كثير 318/1

[5] المواهب اللدنية بالمنح المحمدية 301/2

“አደም ሩህ ሳይገባባቸዉ በፊት እርሳቸዉ ነብይ ነበሩ። ሌሎች ነብያት ግን በነብይነታቸዉ ወቅትና በተልእኮአቸዉ ዘመን እንጅ ነብይ አልሆኑም።”

ከሀዲስ ተንታኝ ዑለሞች ገለጻ እንደምንረዳዉ ነብያችን ከሌሎች ነብይት በተለየ ሁኔታ ገና በሩህ ዓለም እያሉ የነብይነት ማእረግ ፀድቆላቸዋል፤ፀንቶላቸዋል። እንዲያዉቁትም ተደርጎአል።በላይኛ የመላኢኮች ዓለም ታዉጇል። “ወጀበት” የሚለዉ ቃል “ሰበተት” የሚለዉ አቻ ሲሆን ዕዉን መሆንን፣መረጋገጥን፣መፅናትን ያመለክታል። ይህ መልእክት ነብይነታቸዉ በአላህ ዘንድ ከመታወቅ ከፍ ያለ ትርጉም አለዉ። መታወቅማ የእርሳቸዉ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ነብያትም ነብይነት ከአደም በፊት በአዘል ከአላህ ዘንድ ይታወቃል። ስለዚህ የሶሀቦች ጥያቄም ሆነ የሰይዲ መልስ፣እንዲሁም ዑለሞች ሀዲሱን የነብያችንን ብልጫ በሚዘክሩ ምእራፎቻቸዉ ማዉሳታቸዉ ከመታወቅ ከፍ ያለ መልእክት እንዳለዉ ያረጋግጣል። ከዘገባዎች በአንዱ ሰይድ ዑመር “መታጁዒልተ ነብየን” (ነብይ የተደረግከዉ መቼ ነዉ?” በማለት እንደጠየቁቸዉ መተላለፉ ሀዲሱ የአላህን እዉቀት ሳይሆን በተጨባጭና በተግባር ነብይ መደረግን ለማወጅ የተነገረ መሆኑን የበለጠ ያረጋግጣል።

ስለዚህ ከሌሎች ነብያት በተለየ ሁኔታ በሩህ ዓለም የነብይነት ሹመት ነበራቸዉ። ሲወለዱም ነብይ ሆነዉ ተወልደዋል። ከልጅነት እስከዕዉቀትም የነብይነትን ማዕረግ ተጎናፀፈዉ አድገዋል። በ43 ዓመታቸዉ “ኢቅራእ” መባላቸዉ ያን በአዘል የተሰጠ፣በሩህ ዘመን የተነገረ፣ከአባታችን አደም በፊት በመላኢኮች ዓለም የታወጀ ማዕረግ በጀሰድ ዓለም የሚያበስርና የሚያፀና እንጅ አዲስ ሹመት አይደለም። ይህ እንደረፋድ ፀሀይ ከዑለሞች ዘንድ የታወቀ እውነታ ነዉ። ኢማም ቁርጡቢ የሹራ ምእራፍን አንቀፅ 52ን ሲፈስሩ በዚህ ረገድ በርካታ ገጾችን የፈጀ መረጃና ትንታኔ ካቀረቡ በኋላ የሚከተለዉን ደምድመዋል፡-

وأنه صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ مُؤْمِنًا بِاللَّهِ عَزَّ وَجَلَّ، وَلَا سَجَدَ لِصَنَمٍ، وَلَا أَشْرَكَ بِاللَّهِ، وَلَا زَنَى وَلَا شَرِبَ الْخَمْرَ، وَلَا شَهِدَ السَّامِرَ وَلَا حَضَرَ حِلْفَ الْمَطَرِ وَلَا حِلْفَ الْمُطَيَّبِينَ بَلْ نَزَّهَهُ اللَّهُ وَصَانَهُ عَنْ ذَلِكَ[6]

“(ከነብይነታቸዉም በፊት) በሀያሉና በተላቀዉ አላህ ያምኑ ነበር። ለጣኦት ፈፅሞ አልሰገዱም። በአላህም ፈፅሞ አላጋሩም። ዝሙት ፈፅሞ አልሰሩም። አስካሪ መጠጥ ፈፅሞ አልቀመሱም። ከማዕዱም አልተገኙም። ከመሀይምነት ዘመን የግፍ ዉሎችና ህብረቶች ዉስጥም አልተሳተፉም። አላህ ከዚህ ሁሉ ጠብቋቸዋል።”

[6] الجامع لأحكام القرآن = تفسير القرطبي 58/16

ኢማም አል በገዊም ተመሳሳይ እይታቸዉን አጋርተዋል።

وَأَهْلُ الْأُصُولِ عَلَى أَنَّ الْأَنْبِيَاءَ عَلَيْهِمُ السَّلَامُ كَانُوا مُؤْمِنِينَ قَبْلَ الْوَحْيِ، وَكَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَعْبُدُ اللَّهَ قَبْلَ الْوَحْيِ عَلَى دِينِ إِبْرَاهِيمَ، وَلَمْ يَتَبَيَّنْ لَهُ شَرَائِعُ دِينِهِ.

“የዐቂዳ ሊቃዉንት እንዳፀኑት ነብያት ሁሉ ወህይ ሳይወርድላቸዉ በስተፊትም ሙእሚኖች ነበሩ። ነብዩ (ሶ ዐ ወ) ከወህይ በፊት በኢብራሂም ዲን አላህን ያመልኩ ነበር። ያንየ የርሳቸዉ ዲን ህግጋት አልተብራራላቸዉም ነበር።”[7]

ሌሎች ሊቃዉንትም ተመሳሳይ ሀሳብ ሰንዝረዋል።[8] ይህ የአህሉሱና ዐቂዳ ከቁርአንና ከሀዲስ መልእክቶች በተጨማሪ የነብያችንን አጠቃላይ ህይወት በወጉ ከማጥናት የመነጨ ነዉ። እርሳቸዉ ራሳቸዉ ስለአስተዳደጋቸዉና በልጅነት እድሜ ስለጣኦታት የነበራቸዉን ስሜት ሲገልፁ፡-

(بُغِّضَتْ إِلَيَّ الْأَصْنَامُ)[9]

“ጣኦታትን እንድጠላ ተደርጊያለሁ።”

ከሲራ ኪታቦች ዉስጥ እንደሰፈረዉ በልጅነታቸዉ ከአጎታቸዉ አባጣሊብ ጋር ወደሻም በሄዱ ጊዜ የነብይነት ምልክት ያየባቸዉ በሂራ የተባለ መነኩሴ “ላትና ዑዛ” በተባሉ ጣኦታት እንዲምሉ በጠየቃቸዉ ጊዜ ተከታዩን ምላሽ ሰጡት፡

(لَا تَسْأَلْنِي بِهِمَا فَوَاللَّهِ مَا أَبْغَضْتُ شَيْئًا قَطُّ بُغْضَهُمَا)[10]

“በነርሱ አታስምለኝ፤እነርሱን የምጠላዉን ያህል ሌላ ነገር ጠልቼ አላዉቅም፤”

የልጅነት ስብእናቸዉ በዚህ መልኩ የታነፀ ነበር።[11] ገና በልጅነቱ በበኒ ሰዕድ መስክ በመላኢኮች አማካይነት ቀዶ ጥገና ተደርጎለት ቀልቡ በኑር ታጥቦ በኑር የተሞላ ልዑል ከዚህ ዉጭ ምን ሊሆን ይችላል?

---

[7] معالم التنزيل في تفسير القرآن = تفسير البغوي 201/7

[8] فتح القدير 623/4,

[9] الشفا بتعريف حقوق المصطفى 267/2

[10] سيرة ابن إسحاق (كتاب السير والمغازي) : محمد بن إسحاق بن يسار المطلبي بالولاء، المدني75/1

[11] الجامع لأحكام القرآن = تفسير القرطبي 96/20

- እርሳቸዉ በኩፍር ላይ ሊሆኑ ይቅርና ጥቃቅን ስህተት እንኳ ከመፈጸም አላህ ሲጠብቃቸዉ ኖሯል። ገና ልጅ እያሉ ልባቸዉ በኑር ታጥቦ፣ጥበብና ብርሀን ተሞልቷል። በአዘል የመጥፎ ነገር ዝንባሌ ከማንነታቸዉ በኖ ጠፍቷል። ሰይዲ እንዲህ ሲሉ ይህን ነጥብ አረጋግጠዋል፡-

لَمَّا نَشَأَتُ بُغِّضَتْ إِلَيَّ الْأَوْثَانُ وَبُغِّضَ إِلَيَّ الشِّعْرُ[12] وَلَمْ أَهُمَّ بِشَيْءٍ مِمَّا كَانَتِ الْجَاهِلِيَّةُ تَفْعَلُهُ إِلَّا مَرَّتَيْنِ فَعَصَمَنِي اللَّهُ مِنْهُمَا ثُمَّ لَمْ أَعُدْ[13]

“ጣኦታትንና ቅኔን የምጠላ ሆኜ ነዉ ያደግኩት፤የጃሂልያ ዘመን ሰዎችን ድርጊቶች ከሁለት አጋጣሚዎች ዉጭ አስቤ የማላዉቅ ሲሆን በሁለቱም ጊዚያት አላህ ጠበቀኝ። ከዚያ በኋላ ጭራሹኑ አልተመለስኩም፤”

- ካህድያን ነብያችንን “ዉሸታም ደጋሚ ወዘተ” እያሉ ለአድማጩ እዉነት የሚመስሉ የክስ መዐቶችን ደርድረዉባቸዋል። ጥቃቅን ነገሮችን ሳይቀር እየተከታተሉ ለማነወር ሞክረዋል። ለምሳሌ ቂብላ ከበይተል መቅዲስ ወደካዕባ ሲቀየር “ለምን ሆነ?” በማለት አየሩን በጨኸት ሞልተዉታል። አንድም ጊዜ ግን “ጥንት ትከተለዉ የነበረዉን ሀይማኖት አስተባበልክ” ብለዋቸዉ አያዉቁም። ምክንያቱም ይህን እንዲሉ የሚያስችላቸዉ አንድም የህይወት አጋጣሚ ከልጅነት እስከ እዉቀት ስለሌለ። ከዚህ ይልቅ “አባቶቻችን ሲከተሉት የነበሩትን እምነት ተቸህ” ነበር ቅያሚያቸዉ። በልጅነታቸዉ ለቅፅበት እንኳ በዚህ የጥፋት ጎዳና አልፈዉ ቢሆን ኖሮ ለቁረይሾች አሪፍ አጋጣሚ ነበር። “ትላንት አንተ ተዘፍቀህበት የነበረዉን ነገር እንዴት ዛሬ ታወግዘዋለህ?” በማለት ለማሳቀቅ ያመቻቸዉ ነበር። ኢማም ቃዲ ዒያድ እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል፡

إِنَّ قُرَيْشًا قَدْ رَمَتْ نَبِيَّنَا عَلَيْهِ السَّلَامُ بِكُلِّ مَا افْتَرَتْهُ، وَعَيَّرَ كُفَّارُ الْأُمَمِ أَنْبِيَاءَهَا بِكُلِّ مَا أَمْكَنَهَا وَاخْتَلَقَتْهُ، مِمَّا نَصَّ اللَّهُ عَلَيْهِ أَوْ نَقَلَتْهُ إِلَيْنَا الرُّوَاةُ، وَلَمْ نَجِدْ فِي شَيْءٍ مِنْ ذَلِكَ تَعْيِيرًا لِوَاحِدٍ مِنْهُمْ بِرَفْضِهِ آلِهَتَهُمْ وَتَقْرِيعِهِ بِذَمِّهِ بِتَرْكِ مَا كَانَ قَدْ جَامَعَهُمْ عَلَيْهِ. ولو كان هذا لكانوا بذلك مبادرين، ويتلونه فِي مَعْبُودِهِ مُحْتَجِّينَ، وَلَكَانَ تَوْبِيخُهُمْ لَهُ بِنَهْيِهِمْ عَمَّا كَانَ يَعْبُدُ قَبْلُ أَفْظَعَ وَأَقْطَعَ فِي الْحُجَّةِ مِنْ تَوْبِيخِهِ بِنَهْيِهِمْ عَنْ تَرْكِهِ آلِهَتَهُمْ وَمَا كَانَ يَعْبُدُ آبَاؤُهُمْ مِنْ قَبْلُ،

[12] شرف المصطفى : عبد الملك بن محمد بن إبراهيم النيسابوري الخركوشي، أبو سعد 447/1

[13] الجامع لأحكام القرآن = تفسير القرطبي 56/16

فَفِي إِطْبَاقِهِمْ عَلَى الْإِعْرَاضِ عَنْهُ دَلِيلٌ عَلَى أَنَّهُمْ لَمْ يَجِدُوا سَبِيلًا إِلَيْهِ، إِذْ لَوْ كَانَ لَنُقِلَ وَمَا سَكَتُوا عَنْهُ كَمَا لَمْ يَسْكُتُوا عَنْ تَحْوِيلِ الْقِبْلَةِ وَقَالُوا" مَا وَلَّاهُمْ عَنْ قِبْلَتِهِمُ الَّتِي كانُوا عَلَيْها"[14]

“አላህ እንደነገረንና በታሪክ እንደተላለፈልን ቁረይሾች በመልእክተኛዉ ላይ በርካታ የቅጥፈት ክሶች ሰንዝረዋል። ሌሎች ከሀድያን ህዝቦችም ነብያቶቻቸዉን በፈበረኳቸዉ ዉሸቶች አነዉረዋል። ሆኖም ከቅጥፈት ክሶቻቸዉ መካከል “ከአሁን ቀደም አብረን እንፈፅመዉ የነበረዉን የአማልክቶቻችንን አምልኮ እንዴት አሁን ታነዉራለህ?” የሚል አንድስ እንኳ ክስ አይገኝበትም። ነብያቱ እንዲህ አይነት የቀደመ ተሳትፎ ቢኖራቸዉ ኖሮ ካህድያኑ ከመጥቀስ ወደኋላ አይሉም። በመረጃ ረገድም “አባቶቻችን ያመልኳቸዉ የነበሩ አማልክቶቻችንን ለምን ተዉ ትለናለህ” ከሚለዉ ይልቅ “አንተ ራስህ ስታመልካቸዉ የነበሩትን ለምን ታጣጥላለህ” የሚለዉ ይበልጥ ጠንካራ ነዉ። በሁሉም ዘመናት የኖሩ ካህድያን ይህን ጉዳይ ባለማንሳት መስማማታቸዉ መግቢያ ቀዳዳ ላለማግኘታቸዉ መረጃ ነዉ። አግኝተዉ ቢሆን ኖሮ ወደኛ ይተላለፍ ነበር። ቂብላ ሲቀየር ዝም እንዳላሉትና “ ከነበሩበት ቂብላ ምን አስዞራቸዉ?” በማለት እንዳነወሩት ሁሉ ይህንንም በዝምታም አያልፉትም ነበር።”

ለሶሀቦች ከላይ የተዘረዘሩ ዕዉነታዎች ልጆቻቸዉን የሚያዉቁትን ያህል ግልፅ ስለነበሩ የአንሳሩ ሶሀባና የወለላዉ (ሶ ዐ ወ) ባለቅኔ ሀሳን እብን ሳቢት እንዲህ ሲል ተቀኝቷል፡-

خلقت مبرء من كل عيب كأنك قد خلقت كما تشاء

“አንተ በፈለግከዉ ሁኔታ የተፈጠርክ ይመስል **ከነዉር ሁሉ የፀዳህ ሆነህ ተፈጠርክ።”**

“ገና ስትፈጠር ጀምሮ ከነዉር የፀዳህ ነህ” ይላቸዋል ይህ ሶሀባ። ትልቁ ነዉር ደግሞ የኩፍር ነዉር ነዉ። የሽርክ ነዉር ነዉ። የጃሂልያ ነዉር ነዉ። ሰይዲ (ሶ ዐ ወ) ከዚህ የገዘፈ ቆሻሻ ይቅርና ከጥቃቅኑም ጉድፍ ጥንፍፍ፣ንፅት ብለዉ ተኸልቀዉ፣በትንግት አጀብ ወደዚህች ዓለም መጥተዉ በጻዕዳነት አድገዋል። የዳናዉ ሸኽ ሚስባህ ይህንኑ የሶሀቦች ዐቂዳ እንዲህ በግጥም ገልፀዉታል፡-

ጥንፍፍ የጥንፍፍ ልጅ በናቱም ባባቱ፤

ዉልዉልም የለዉ መድሀኒትነቱ፤

[14] الشفا بتعريف حقوق المصطفى 258/2

የሀበሻ ዓሊሞች ይህን ዐቂዳ ሲያስተምሩና ሲዘክሩ ኖረዋል። እናማ እርሳቸዉን "ሰለምቴ" ማለት 'አላህ ላልሰለመ ሩህና ገላ የነብይነት ማእረግ አሸከመ' ማለት ስለሆነ፣"ከነዉር ሁሉ የፀዳህ ሆነህ ተፈጠርክ" ያሉ ሶሀቦችን እንደዉሸታም መቁጠር ስለሆነ፣ይህንን አባባል ሰምተዉ ያፀደቁትን ነብይ ሀሰት የሆነን ነገር እንዳፀደቁ የሚያስቆጥር ስለሆነ የከበደ የ"ዐቂዳ" ስህተት ነዉ። "ዑዝር ቢልጀህል" የሚባል ጥንቃቄ ስላለ እንጅ ወደኩፍርም ያደርሳል።

በተላከልኝ ቪዲዮ የተነገረዉን የ"ዐቂዳ" እንከን ለመረዳት እስከዚህ ድረስ የተጻፈዉ በቂ ነዉ። ሆኖም ነገሩ ከተነሳ አይቀር ጥቂት ነጥቦች ባክል አይከፋም።

1. እርሳቸዉ ቀርቶ ሌሎች ነብያትም ክህደት አያዉቃቸዉም። ኢማም ቁርጡቢን ልጥቀስ

وَالصَّوَابُ أَنَّهُمْ مَعْصُومُونَ قَبْلَ النُّبُوَّةِ مِنَ الْجَهْلِ بِاللَّهِ وَصِفَاتِهِ وَالتَّشَكُّكِ فِي شَيْءٍ مِنْ ذَلِكَ. وَقَدْ تَعَاضَدَتِ الْأَخْبَارُ وَالْآثَارُ عَنِ الْأَنْبِيَاءِ بِتَنْزِيهِهِمْ عَنْ هَذِهِ النَّقِيصَةِ مُنْذُ وُلِدُوا، وَنَشْأَتِهِمْ عَلَى التَّوْحِيدِ وَالْإِيمَانِ، بَلْ عَلَى إِشْرَاقِ أَنْوَارِ الْمَعَارِفِ وَنَفَحَاتِ أَلْطَافِ السَّعَادَةِ، وَمَنْ طَالَعَ سِيَرَهُمْ مُنْذُ صِبَاهُمْ إِلَى مَبْعَثِهِمْ حَقَّقَ ذَلِكَ[15]

"ትክክለኛዉ አስተሳሰብ ከነብይነታቸዉ በፊት አላህንና ባህሪያቱን ካለማወቅ፣በዚህ ረገድም ከሚኖር ጥርጣሬ የተጠበቁ ናቸዉ። ነብያት ከተወለዱበት ዕለት ጀምሮ ከዚህ ጉድለት የፀዱና በተዉሂድና በኢማን ፋፍተዉ፣በጥበብ ብርሀን ደምቀዉ፣በሀሴት ፀዳል ተዉበዉ ያደጉ መሆናቸዉን የሚያረጋግጡ መረጃዎች በርካታ ናቸዉ። ከልጅነት እስከ ነብይነት ታሪካቸዉን በወጉ የፈተሸ ይህንኑ ያረጋግጣል።

ቁርአን ዉስጥ የሰፈሩ የነብያት ታሪኮች የሚያረጋግጡት ይህንኑ ነዉ። አላህ ስለ ነቢ የህያ እንዲህ ብሏል

وَآتَيْنَاهُ الْحُكْمَ صَبِيًّا[16]

የተፍሲር ሊቃዉንት እንደሚሉት[17] የህያ በልጅነታቸዉ የአላህን ኪታብ እዉቀት ተችረዋል። ገና የሁለት አመት ልጅ እያሉ ህጻናት ለጫወታ ሲጋብዙአቸዉ "የተፈጠርኩት ለጨዋታ ነዉን?"

[15] المرجع السابق 55/16

[16] መርየም 12

[17] ኢማም ቁርጡቢ ለ አል ሹራ 52 ከሰጡት ትንታኔ የተወሰዱ

በማለት መልሰዋል።ገና የሶስት አመት ልጅ እያሉ በኢሳ ነብይነት ማመናቸዉ ይነገራል። በቁርአን እንደተገለፀዉ ኢሳ ገና እንደተወለዱ እንዲህ ተናግረዋል

إِنِّي عَبْدُ اللَّهِ آتانِيَ الْكِتابَ وَجَعَلَنِي نَبِيًّا[18]

ነቢ ሱለይማን ንጉስ የሆኑት በ12 አመታቸዉ ነበር። ያንየ ጥበብ የተሞላበት ፍርድ መስጠታቸዉንና እዉቀትና ጥበብ እንደተቸራቸዉ ቁርአን ሲገልፅ

فَفَهَّمْناها سُلَيْمانَ وَكُلًّا آتَيْنا حُكْماً وَعِلْماً[19]

ሙሳ በህጻንነታቸዉ የፊረአዉንን ጺም በመጎተት ጥላቻቸዉን አሳይተዋል። ኢብራሂምን በተመለከተ የተነገረዉ የሚከተለዉ የቁርአን መልእክት በልጅነታቸዉ በቀናዉ ጎዳና ላይ እንደበሩ የሚያመለክት ነዉ።

وَلَقَدْ آتَيْنا إِبْراهِيمَ رُشْدَهُ مِنْ قَبْلُ[20]

ወደእሳት ሲጣሉ 16 አመታቸዉ ነበር። ከዋክብትን መነሻ አድርገዉ የህዝባቸዉን እምነት ሲሀይሱ 15 አመታቸዉ ነበር። ዩሱፍ ጉድጓድ ዉስጥ በተጣሉ ጊዜ ወህይ ወርዶላቸዋል።

وَأَوْحَيْنا إِلَيْهِ لَتُنَبِّئَنَّهُمْ بِأَمْرِهِمْ[21]

የሌሎች ነብያት የህይወት ዉሎም እንደዚሁ ነዉ። ኢማም ቃዲ ኢያድ እንዲህ ይላሉ

وَلَمْ يَنْقِلْ أَحَدٌ مِنْ أَهْلِ الْأَخْبَارِ أَنَّ أَحَدًا نُبِّئَ وَاصْطُفِيَ مِمَّنْ عُرِفَ بِكُفْرٍ وَإِشْرَاكٍ قَبْلَ ذَلِكَ[22]

“በክህደትና በሽርክ ዉስጥ የነበረ ሰዉ ለነብይነት የተመረጠበት አንድም አጋጣሚ አልተዘገበም።”

2. ነብያችን ይቅርና ከሰይዱና አደም ጀምሮ ያሉ አያቶቻቸዉ ከዝሙትና ከኩፍር የተጠበቁ ናቸዉ። ለዚህ ዋቢ ይሆን ዘንድ ለሚከተለዉ የቁርአን መልእክት በእብን ዐባስ የተሰጠዉን ተፍሲር ልግለፅ፡-

[18] መርየም 30
[19] አልአንቢያእ 79
[20] አልአንቢያእ 51
[21] ዩሱፍ 15
[22] المرجع السابق 56/16

وَتَوَكَّلْ عَلَى الْعَزِيزِ الرَّحِيمِ الَّذِي يَرَاكَ حِينَ تَقُومُ وَتَقَلُّبَكَ فِي السَّاجِدِينَ

‹‹አሸናፊ አዛኝ በኾነው (ጌታህ) ላይም ተጠጋ፡፡ በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ፡፡ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)፡፡››[23]

እዚህ አንቀጽ ላይ ‹‹በሰጋጆች ዉስጥ›› እና ‹‹መዘዋወርህን›› የሚሉ ሀሳቦችን በተመለከተ የሚከተሉትን ተፍሲሮች እናገኛለን፡-

- ሶላት ዉስጥ ብቻህን ወይም ከሌሎች ሰጋጆች ጋር ሆነህ- ቀታዳ፣ዐጣእ፣ሀሰነል በስሪና ሌሎችም እንደፈሰሩት፤[24]
- ከተከታዮችህ መሀል የሌሊት ሶላት ተሳታፊዎችን ለማየት ስትዘዋወር፤[25]
- ሶላት ዉስጥ ሆነህ ከኋላ የሚሰግዱትን ስትቃኝ፤ነብዩ ﷺ ከኋላቸዉም በኩል ያዩ ስለነበር- ሙጃሂድ፤[26]
- መልዕክትህን ለማድረስ በአማኞች መሀከል ወይም ከነርሱ ጋር ሆነህ ስትዘዋወር-የእብን ዐባስና የቀታዳ ተፍሲር፤[27]
- ልክ እንደሌሎች ነብያት መልዕክትህን ስታደርስ-ጦበራኒ፣በዛር፣አቡ ኑዐይምና ሌሎችም፤[28]

ከላይ በተጠቀሱት ተፍሲሮች ‹‹ሳጂዲን›› የተባሉት ከሶላት ዉስጥ ወይም ዉጭ ያሉ አማኞች፣ ወይም ደግሞ ነብያት ናቸዉ፡፡ ‹‹መዘዋወር›› ደግሞ ከሶላት ሶላት መሸጋገር፣ሰጋጆችን እየተዘዋወሩ መቃኘት፣ከኋላ የሚሰግዱትን ማስተዋል፣ለዳዕዋ መንቀሳቀስ የሚሉትን ትርጉሞች ይዟል፡፡ የሚከተለዉ የእብን ዐባስ ተፍሲር ደግሞ የተለየ እይታ ያቀርብልናል፡ እጠቅሳለሁ፡-

وأبو نعم عن ابن عباس أيضاً إلا أنه رضي الله تعالى عنه فسر التقلب فيهم بالتنقل في أصلابهم حتى ولدته أمه عليه الصلاة والسلام ، وجوز على حمل التقلب على التنقل في الأصلاب أن يراد بالساجدين المؤمنون

‹‹አቡ ኑዐይም እንደዘገቡት እብን ዐባስ ‹‹መዘዋወር›› የሚለዉን ቃል ‹‹ እናታቸዉ አሚና እስክትወልዳቸዉ ድረስ በየትዉልድ ማህጸንና ጀርባ (አስላብ) የተደረገዉን ቅብብሎሽ ያሳያል››

[23] አል ሹዐራእ 217-219
[24] እብን ከሲር
[25] ሩሀል መዐኒ
[26] ያስፈዉ ምንጭ
[27] ያስፈዉ ምንጭ
[28] ያስፈዉ ምንጭ

ብለዋል፡፡ መዘዋወር -በርሳቸዉ አተረጓጎም የትዉልድ ቅብብሎሽ ሲሆን ‹‹ሳጂዲን›› የተባሉት ደግሞ /በዚህ ቅብብሎሽ ዉስጥ የተሳተፉት/ አማኞች ናቸዉ፡፡››[29]

በዚህ አፈሳሰር መሰረት ሰይዳችን የመጡበት የዘር መስመር በሙሉ ሳጅድ (ሙዕሚን) ነዉ፡፡ እሳቸዉ ይቅርና እስከ አባታችን አደም ድረስ ካሉ አባትና እናቶቻቸዉ መሀል ሰለምቱ የለም፡፡ ሁሉም የተፈጥሮ ሀይማኖታቸዉን ይዘዉ፣በተዉሂድ ፀንተዉ፣በኢማን ደርጅተዉ ነዉ ከዚህች አለም ዉስጥ የኖሩት፡፡ ከዚህ የተለየዉን አስተሳሰብ፣በተለይም “ወላጆቼና ወላጆችህ” የሚለዉን ሀዲስ ትርጉምና ይዘት “የነብዩ ወላጆች መልካም እጣ ፈንታ በቁርአንና በሀዲስ እይታ” በተሰኘ መፅሀፌ ዉስጥ በወጉ ስለተተነተነ እርሱን ማየት ይቻላል፡፡ የሀገራችን ዑለሞች ይህን ዐቂዳህ በየመድሆቻቸዉ ሲያስተጋቡት ኖረዋል፡፡ *ጌታዉ ሸኽ ሚሰባህን* ለናሙና ልጥቀስ፡፡ *‹‹ነቢ ዘይኔ››* ላይ እንዲህ አዚመዋል፡-

‹በጡሀራ ማጠን የተረማመደዉ፤

ዓይኖቹን ተኩሎ ነዉ የተወለደዉ፤

እናማ ሰይዲ ይቅርና በዘራቸዉ ጅል ነገር አይታወቅም፡፡

3. አላህ በሱረቱ አለ ዒምራን 81 ላይ ከአባታችን አደም ጀምሮ የመጡ ነብያትን እያንዳንዳቸዉን በአሸረፈል ኸልቅ እንዲያምኑና እንዲከተሉ ቃል ማስገባቱን በተመለከተ ኢማም አል ሀፊዝ ጀላሉዲን ሱዩጢ በሰጡት ማብራሪያ ላይ “ድሮ ድሮ (ልጅ እያሉ ይመስለኛል) እንዲህ እናስብ ነበር” በማለት የሀሳብ ስህተታቸዉን ለማረም ሁለት ጠቃሚ ነጥቦችን አንስተዋል፡፡ እጠቅሳለሁ፡-

أَحدهمَا قَوْله صلى الله عَلَيْهِ وَسلم بعثت إِلَى النَّاس كَافَّة كُنَّا نظن انه من زَمَانه إِلَى يَوْم الْقِيَامَة فَبَان انه جَمِيع النَّاس أَوَّلهمْ وَآخرهمْ وَالثَّانِي قَوْله صلى الله عَلَيْهِ وَسلم كنت نَبيا وآدَم بَين الرّوح والجسد كُنَّا نظن أَنه بِالْعلمِ فَبَان أَنه زَائِد على ذَلِك مَا شرحناه[30]

[29] ያስፈዉ ምንጭ

[30] الخصائص الكبرى جلال الدين السيوطي 11/1

“አንደኛዉ ነጥብ ነብዩ (ሶዐወ) ‘ለሰዉ ልጆች ሁሉ ተልኪያለሁ’ ማለታቸዉን ከርሳቸዉ ዘመን ጀምሮ እስከቂያማ ድረስ ላለዉ ሰዉ ብቻ የተላኩ አድርገን እንገምት ነበር። በኋላ ግን ከመጀመሪያዉ ሰዉ እስከመጨረሻዉ ለሰዉ ልጆች ባጠቃላይ መላካቸዉን ተረዳን። ሁለተኛዉ ነጥብ ‘አደም በሩህና በጀሰድ መካከል ሆኖ እያሉ ነብይ ነበርኩ’ የሚለዉን ንግግራቸዉን በዕዉቀት (አላህ ነብይነታቸዉን ያንጊዜ ያዉቅ ነበር) ማለት እንደሆነ እንገምት ነበር። በኋላ ግን ከዚህ በላይ የሆነ መልዕክት እንዳለዉ ተረዳን።”

የሚገርመዉ እኔም ልጅ እያለሁ እነዚህኑ ስህተቶች ተሳስቻለሁ። ነብያችን ለሰዉ ልጆች ሁሉ የተላኩ ናቸዉ ሲባል ከ14 ክፍለዘመናት ወዲህ ላሉት የሰዉ ልጆች ብቻ ይመስለኝ ነበር። ለካስ ሹመታቸዉ ዳርና ድንበር የለዉም። “አደም በሩህና በጀሰድ መካከል ሆነዉ እያለ ነብይ ነበርኩ” ሲሉም “አላህ ነብይነቴን ያዉቃል” ለማለት ፈልገዉ ይመስለኝ ነበር። መልእክቱ ከዚህም የላቀ መሆኑን የተረዳሁት ዘግይቶ ነዉ። ምክንያቱም አላህ የርሳቸዉን ነብይነት የሚያዉቀዉ ከአባታችን አደም በፊት በአዘል ነዉ። ደግሞም ይህን ሀዲስ የጠቀሱት እርሳቸዉ ከሌሎች ነብያት ያላቸዉን ብልጫ ለመጥቀስ ሲሆን ነገሩን በእዉቀት ከፈሰርነዉ አላህ የሌሎች ነብያትንም ነብይነት በአዘል ስለሚያዉቅ ከሌሎች የተለዩ አያደርጋቸዉም። የሶሀቦችም ጥያቄ ላግጣ ይሆናል። ምክንያቱም “አላህ የእርስዎን ነብይነት የሚያዉቀዉ መቼ ነዉ?” በማለት እንደጠየቁ ያስመስላል። ከላግጣም በላይ ኩፍር ነዉ። የአላህን የአዘል እዉቀት ከጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባ ነዉና። የነብያችን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ይህን ስህተት ፈፅሞ ሊሳሳቱ አይችሉም። የሶሀቦች ጥያቄ ግን በጥንቃቄ የተዋቀረ ነዉ። “ወጀበት” የሚል ቃል ነዉ የተጠቀሙት። “ነብይነት የፀናለዎት (የተረጋገጠልዎት) መቼ ነዉ?” መልሳቸዉን ከላይ ስላብራራሁ አልደግመዉም።

4. በጥቅሉ ከሰይዳችን ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ እጅግ የበዛ ጥንቃቄ ይሻል። ዘወትር ማንበብንም ይፈልጋል። እንዲያም ሆኖ አያልቅም። ተዋኝቶ አይዘለቅም። ለዚያ ነዉ የሀበሻዉ የቅኔ አዉራ ሰይድ ጫሌ እድሜ ልካቸዉን ስለወለላዉ ነብይ (ሶዐወ) ሲቀኙና ሲተነትኑ ከኖሩ በኋላ እንዲህ በማለት አቅመቢስነታቸዉን የገለፁት፣

غصنا في البحر طويل القعر

لكن ما ندري له طرفا

በግርድፉ ወደአማርኛ ሲመነዘር፡

ዋና ወጠንን ከባህር ከጥልቅ

ወሰን ዳርቻዉ ከማይታወቅ

በሌላ ግጥማቸዉም እንዲህ ተቀኝተዋል

ላዩን ነገርኩህ ተወኝ ሚስጥሩን

ኑን ወልቀለሚ ወማየስጡሩን

እንዲህም ስለሆነ ብዙ ዑለሞች የሰይዲን ጉዳይ በቃላት ክምር፣በቅኔ ድምር በትክክል መግለፅ እንደማይቻል ገብቷቸዉ ስሜታቸዉን ወደዉስጥ ቀብረዉ መብሰልሰልን ይመርጣሉ። ሀያታቸዉን በ"ታጁል ሙርሰላ" የጨረሱት የጀማሉዲን አልአኒ ተማሪ ሸኽ ሙሀመድ አመዴ የነቢን አፍቃሪዎች ሁሉ በመወከል ይህን እንቆቅልሽ እንዲህ ገልፀዉታል፣

قد حفروا قبرا في ميدان الحشا

ودفنوا فيها أسرارا لاتفشى

ትርጉሙ፡-

ከሆዳቸዉ ሜዳ ቆፍረዉ መቃብር

ሚስጥር ቀበሩበት ይፋ ማይነገር

አዎ፣ለሰዉ የማይነገር ስንት ህመም፣ስንቱ ቁስል፣ስንት ሚስጥር አለ። በአንድ በኩል ቃላት ጉልበት ስለሌላቸዉ፣በሌላ በኩል አድማጩ የታማሚዉን ያህል ህመሙ ዘልቆ ስለማይገባዉ።

እንደማሳረጊያ

ከላይ ከተብራራዉ መሠረታዊ እሳቤ የተለየ ይዘት ያላቸዉ የሚመስሉ የቁርአን ወይም የሀዲስ መልዕክቶችን በጥንቃቄ ማየትና መረዳት እንደሚያስፈልግ ሳላሳስብ ዕሁፌን ማሳረግ ጎደሎ እንዳያደርገዉ ስለሰጋሁ አንዲት ናሙና ብቻ አሳይቼ ልሰናበት። አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَوَجَدَكَ ضَالًّا فَهَدَى

"የሳትክ ሆነህ አገኘህና መራህ" (ዱሀ 7)

ከዚህች አንቀፅ ላይ (ضَالًّا) (የሳትክ) የሚለዉን “ጠማማ” ብሎ መፈሰር አሳሳች ነዉ። ምናልባትም “ሰለምቴ” የሚለዉ የዐቂዳ ጉድፍ የመነጨዉ ከዚህች ሳይሆን አይቀርም። “ضَالًّا“ በቁርአን ተንታኞች ዘንድ ከ 10 ያላነሱ ትርጉሞች ተሰጥተዉታል። አንዳቸዉም ግን ከጅል ነገር ጋር የተገናኙ አይደሉም። የኢማም ቁርጡቢን ተፍሲር[31] ተንተርሰን ዋና ዋናዎቹን ባጭሩ ለማየት ያህል፡-

1. <u>በነብይነት ስለሚጠበቅብህ ሀላፊነት ዝርዝር መረጃ የሌለህ ሆነህ አገኘህ፡-</u> ወለላዬ (ሶ ዐ ወ) ገና በሩህ ዐለም ነብይ ተደርገዉ ቢሾሙም ዝርዝር ሀላፊነታቸዉ ገና አልተነገራቸዉም። ወይም በዘመኑ አገላለፅ ሀላፊነት እንደተጣለባቸዉ አወቁ እንጅ የሥራ መዘርዝር አልተሰጣቸዉም።

أَيْ غَافِلًا عَمَّا يُرَادُ بِكَ مِنْ أَمْرِ النُّبُوَّةِ، فَهَدَاكَ: أَيْ أَرْشَدَكَ. وَالضَّلَالُ هُنَا بِمَعْنَى الْغَفْلَةِ،

“ስለነብይነት ጉዳይ መረጃዉ አልነበረህም። እናም ወደርሱ መራህ። እዚህ ላይ “ዶላል” የሚለዉ ቃል “ገፍላ” (የመረጃ አለመኖር) ማለት ነዉ።”

2 **ስለቁርአንም ሆነ የእስልምና እምነት ስለያዛቸዉ ዝርዝር ህግጋቶች <u>መረጃ የሌለህ ሆነህ አገኘህ</u>፡-** ወለላዬ (ሶ ዐ ወ) ገና በሩህ ዐለም ነብይ ተደርገዉ ቢሾሙም ስለሚላክላቸዉ ቁርአንም ሆነ ስለዝርዝር ህግጋቱ የተነገራቸዉ በ23 ዓመታት የጊዜ ሂደት ዉስጥ ነዉ። የኢማም እብን ከሲር ምርጫ ይህኛዉ ነዉ።[32]

لَمْ تَكُنْ تَدْرِي الْقُرْآنَ وَالشَّرَائِعَ، فَهَدَاكَ اللَّهُ إِلَى الْقُرْآنِ، وَشَرَائِعِ الْإِسْلَامِ،[33]

“ቁርአንንም ሆነ ዝርዝር የሸሪዐዉ ህግጋትን በተመለከተ መረጃዉ አልነበረህም። እናም አላህ ወደቁርአንና ወደእስልምና ሸሪዐ መራህ።”

[31] ተፍሲር ቁርጡቢ 20/96-99

[32] تفسير القرآن العظيم 8–426

[33] الجامع لأحكام القرآن = تفسير القرطبي 97/20

3 **መንገድ በሳተ፣ያንተን እምነት በማይከተል ህዝብ መሀል ብቸኛ ሆነህ አገኘህ፡-** በዚህ አፈሳሰር መሠረት ቃሉ የሚመለከተዉ እርሳቸዉን ሳይሆን ህዝባቸዉን ነዉ። "መንገድ ከሳቱት መሀል አግኝቶ ለነርሱ መቀናት አንተን ሰበብ በማድረግ ዉለታ ዉሎልሀል" ማለት ነዉ።

وَوَجَدَكَ ضَالًّا أَيْ فِي قَوْمٍ ضُلَّالٍ، فَهَدَاهُمُ اللَّهُ بِكَ.[34]

"አላህ መንገድ በሳቱ ህዝቦች ዉስጥ ባንተ አማካይነት እነርሱን አቀና፣"

4 **አፍቃሪ ሆነህ አገኘህና ወደፍቅሩ መራህ፡-** ቃሉ ፍቅርንም ያመለክታል። ወዳጀ ከአዘል የመቀናትን ፍቅር ተግተዋል። ልባቸዉን በኑር ሞልተዋል። እናም አላህ ወደመቀናት በወሀዩ መራቸዉ። ለኔ ይህኛዉ አፈሳሰር ይበልጥ ይስበኛል።

وَوَجَدَكَ مُحِبًّا لِلْهِدَايَةِ، فَهَدَاكَ إِلَيْهَا،[35]

''የመቀናት አፍቃሪ ሆነህ አገኘህ፣ወደርሱም መራህ፤"

5. "በመካ ጠለቆዎች መንገድ ስተህ አገኘህ፤ ከአደጋ ጠብቆ ከወገኖችህ ጋር አገናኘህ፤" ተብሎም ተፈስሮአል። እብን ዐባስ እንዳስተላለፉት። በሂጅራ ጊዜ መንገድ ስተዉ አቅጣጫ መምራቱን ለማመልከት ነዉም ተብሎአል።
6 "ضَالٌّ " ተብሎም በ"ረፍዕ" ተቀርቷል። በዚህ አቀራር መሰረት "መንገድ የሳቱ ህዝቦች አገኙህና ባንተ ተቀኑ" ይሆናል ተፍሲሩ።

وَفِي قِرَاءَةِ الْحَسَنِ وَوَجَدَكَ ضَالٌّ فَهَدَى أَيْ وَجَدَكَ الضَّالُّ فَاهْتَدَى بِكَ، وَهَذِهِ قِرَاءَةٌ عَلَى التَّفْسِيرِ[36]

7 **የመቀናት (ሂዳያ) ምልክት አደረገህ** ማለትም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም አቅጣጫ በማይታወቅበት አሸዋማ በረሀ ዉስጥ የበቀለች ዛፍ ከዐረቦች ዘንድ (ضَالَّةً) ትባላለች። ሰዎች መንገድ እንዳይስቱ በአቅጣጫ ጠቋሚነት ይጠቀሙባታል። በርሷ ተመርተዉ ካሰቡት ይደርሳሉ። ወለላዬም (ሶ ዐ ወ) እንደዚሁ ናቸዉ። የሂዳያ ምልክት፤የደግነት መምህር፤ የሰብአዊነት አባት፤ ወደጅነት የሚያደርሰዉን መንገድ አመላካች።

[34] المرجع السابق 97/20
[35] المرجع السابق 99/20
[36] المرجع السابق 99/20

إِذَا وَجَدَتِ الْعَرَبُ شَجَرَةً مُنْفَرِدَةً فِي فَلَاةٍ مِنَ الْأَرْضِ، لَا شَجَرَ مَعَهَا، سَمَّوْهَا ضَالَّةً، فَيُهْتَدَى بِهَا إِلَى الطَّرِيقِ، فقال الله تعالى لِنَبِيِّهِ مُحَمَّدٍ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: وَوَجَدَكَ ضَالًّا أَيْ لَا أَحَدَ عَلَى دِينِكَ، وَأَنْتَ وَحِيدٌ لَيْسَ مَعَكَ أَحَدٌ، فَهَدَيْتُ بِكَ الْخَلْقَ إِلَيَّ[37]

“ዐረቦች ከበረሀ መሀል የሚያገኟትን ብቻዋን የቆመች ዛፍ “ዳለህ” በማለት ይጠሯታል። እርሷን ምልክት አድርገዉ አቅጣጫ ያዉቁባታል። አላህም ለነብዩ ‘ብቸኛ ነበርክ። ዲንህን የሚከተል ሰዉ አልነበረም። እናም ባንተ አማካይነት ፍጡራንን መራሁ’ አላቸዉ።”

ኢማም ቁርጡቢ ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉንም ተፍሲሮች “መልካም ናቸዉ” በማለት ከገለፁ በኋላ ለርሳቸዉ የበለጠ የሚያስደስታቸዉ የመጨረሻዉ መሆኑን አስምረዋል፡-

هَذِهِ الْأَقْوَالُ كُلُّهَا حِسَانٌ، ثُمَّ مِنْهَا مَا هُوَ مَعْنَوِيٌّ، وَمِنْهَا مَا هُوَ حِسِّيٌّ. وَالْقَوْلُ الْأَخِيرُ أَعْجَبُ إِلَيَّ، لِأَنَّهُ يَجْمَعُ الْأَقْوَالَ الْمَعْنَوِيَّةَ.[38]

“ሁሉም አፈሳሰሮች መልካም ናቸዉ። ገሚሶቹ ረቂቅ፣ ሌሎቹ ደግሞ ገሀዳዊ ይዘት አላቸዉ። የመጨረሻዉ አፈሳሰር የረቂቅ መልእክቶችን ይዘት ሁሉ ያጠቃለለ በመሆኑ ወድጀዋለሁ።”

በሱረቱ ሹራ አንቀፅ 12 ላይ “ወለል ኢማኑ” የሚለዉን ቃል “አመነትም አልነበረህም” ብሎ መፈሰር አሳሳች ነዉ። ከላይ በዝርዝር እንዳረጋገጥነዉ ነብዩ ከወህይ በፊትም ኢማን ነበራቸዉ። ስለዚህ ከዚህ አንቀፅ ላይ “ኢማን” የተሰኘዉ ዝርዝር የሸሪዐ ድንጋጌ ነዉ።[39] በሌላ የቁርአን አንቀፅ ሶላት “ኢማን” ተብላ እንደተጠራችው።[40] ሌሎች ተመሳሳይ የቁርአን አንቀጾችንም በዚሁ አግባብ መረዳት ተገቢ ነዉ። ዲኑን በተመለከተ ምንጊዜም ጠንቃቀ መሆን ያስፈልጋል። የዲኑ አስኳል የሆኑት የነብያችን (ሶ ዐ ወ) ጉዳይ ደግሞ የበለጠ ጥንቃቄ ይሻል። በኢልሙ ዘርፍ ወፍ ዘራሽ ግንዛቤ አይበተንም።

ለማጠቃለል

“አልዒልሙ ቀብለልቀዉሊ ወልዐመሊ” የተባለዉ ከእንዲህ አይነት ስህተቶች ላይ እንዳንወድቅ ነዉ። ዲኑ በዑለሞች መመራት አለበት የሚባለዉም ለዚሁ ነዉ። እዚህ አገር ላይ “ዐቂዳ” በወጉ መቀራት ካቆመ 30 ዓመታት ተቆጥረዋል። እናም “የተሻሉ” ተደርገዉ ከሚታሰቡ ሰዎች ከዚህም የባሱ ጉድፍ አስተሳሰቦችን ብንሰማ እንዳንገረም።

---

[37] المرجع السابق 99/20

[38] المرجع السابق

[39] تفسير النسفي (مدارك التنزيل وحقائق التأويل) 262/2

[40] አልበቀራህ 143

ይህ አጋጣሚ እስልምና በዘመናዊዉ ዓለም የገጠመዉን ፈተናም በመጠኑ ያሳያል። ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ፣ግና ስለሀይማኖቱ በቂ ወይም ምንም ዕውቀት የሌላቸዉ ሰዎች የሀይማኖቱ ባለቤቶችና አፈቀላጤዎች፣የቁርአንና የሀዲስ ተንታኞች ሆነዉ መከሰታቸዉ ብዙ ነገር አናግቷል። “ዉሀዉ ወደቦዩ” እስኪመለስ ድረስ ከማስተማር በስተቀር ምን አማራጭ አለ? “The Great theft Wrestling Islam from Extremists” የተሰኘዉ የካሊድ አቡልፈድል መፅሀፍ ሊያሳየን የሞከረዉ ይህን አደጋ ነዉ። “ታላቁ ዘረፋ” በሚል ርዕስ በቅርቡ ተተርጉሟል።

አላህ ሀገራችንን ሠላም ያድርግል። የአብሮነትንና የመተሳሰብን ጥበብ ይለግሰን። ህዝባችንን ከክፉ ነገሮች ሁሉ ይጠብቅልን። አላሁም አሚነ።

የመረጃ ምንጮች

المصادر والمراجع

1. القرآن الكريم
2. الجامع لأحكام القرآن: محمد بن أحمد بن أبي بكر بن فرح القرطبي أبو عبد الله
3. تفسير القرآن العظيم: أبو الفداء إسماعيل بن عمر بن كثير القرشي الدمشقي
4. فتح القدير الجامع بين فني الرواية والدراية من علم التفسير: محمد بن علي الشوكاني
5. معالم التنزيل: محيي السنة :أبو محمد الحسين بن مسعود البغوي
6. روح المعاني في تفسير القرآن العظيم والسبع المثاني: شهاب الدين محمود ابن عبدالله الحسيني الألوسي
7. **تفسير النسفي (مدارك التنزيل وحقائق التأويل) أبو البركات عبد الله بن أحمد بن محمود حافظ الدين النسفي**
8. **الجامع :محمد بن عيسى بن سَوْرة بن موسى بن الضحاك، الترمذي، أبو عيسى**
9. **العرف الشذي شرح سنن الترمذي**
10. **التيسير بشرح الجامع الصغي**
11. سنن البيهقي: أحمد بن الحسين بن علي بن موسى أبو بكر البيهقي
12. مسند الإمام أحمد بن حنبل: أحمد بن حنبل
13. **الخصائص الكبرى:أبو الفضل جلال الدين عبد الرحمن أبي بكر السيوطي**
14. .المواهب الدنية: الحافظ قسطلاني
15. البداية والنهاية:إسماعيل بن عمر بن كثير القرشي أبو الفداء
16. **الشفا بتعريف حقوق المصطفى: عياض بن موسى بن عياض بن عمرون اليحصبي السبتي، أبو الفضل**
17. **سيرة ابن إسحاق (كتاب السير والمغازي) : محمد بن إسحاق بن يسار المطلبي بالولاء، المدني**
18. **شرف المصطفى : عبد الملك بن محمد بن إبراهيم النيسابوري الخركوشي، أبو سعد**